የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 13
ADDIS ABABA, 8th January, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፸፬/፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው የወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነት አዋጅ ማፅደቂያ……………………ገጽ ፯ሺ፱፻፳፮

CONTENTS

Proclamation No. 874/2014

Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the government of Republic of Sudan Ratification Proclamation……………Page 7926

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፸፬/፪ሺ፮

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነት ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በካርቱም ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No.874/2014

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF SUDAN ON MUTUAL LEGAL ASSISTANCE IN CRIMINAL MATTERS

WHEREAS, the Agreement Mutual Legal Assistance in Criminal Matters has been signed in Khartoum 4th day of December 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan;

WHEREAS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement in its session held on the 2nd day of December ,2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 9.20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው የወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፸፬/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በካርቱም ከተማ የተፈረመው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትህ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የፍትህ ሚኒስቴር ሥልጣን

የፍትህ ሚኒስቴር የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት በማስተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan Ratification Proclamation No.874/2014".

## 2. Ratification of the Agreement

This Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan on Mutual Legal Assistance in Criminal Matters signed in Khartoum 4th day of December 2013 is here by ratified.

## 3. Power of the Ministry of Justice

The Ministry of Justice, by coordinating other concerned government organs, is hereby empowered to implement this agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of January, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት